" ጠበኛ እውነቶች' በሜሪ ፈለቀ!

( በብሩክ መልኬ )

ካልተሳሳትኩ የመጀመሪያ መፅሃፏ አይደል፣ አንኳን ደስ አለሽ ።  መልካም ነው ማለት እፈልጋለሁ...

በ'ጠበኛ እውነቶች' መጽሐፍ ውስጥ ብዙ መልካም ነገሮችን መጥቀስ ብችልም በዋናነት ከልብ የወደድኩትን አንድ ነገር በዝርዝር ለማጋራት ልሞክር።

በኔ ዕይታ በድርሰትሽ ውስጥ ማጠንጠኛቸው አንድ የሆኑ ተዛማጅ የገፀ-ባህርያት ታሪኮች በብዙ የአማርኛ ልብ-ወለድ ድርሰቶች እንደምናየው በሶስተኛ መደብ ትርክት የተገለፁና ጎን ለጎን ተያይዘው የሚቀጥሉ አንዳንዴም

ተጨማሪ ቅጥያዎችን ከጎን እያስገባ ወደ መስፋት የሚጓዝ ነባር አካሄድን አለመከተሉ በጣም የምወደውን 'ዋና ነገር' እንዳገኝበት አድርጎኛል! እርሱም....ሰፊና ገለልተኛ የምልከታ አድማስ/የዳኝነት መነፀርን ነው፡፡ ምክንያቴ ደግሞ በ'ጠበኛ እውነቶች' ድርሰትሽ ውስጥ ከዳር በመነሳት ወደ መሀል የሚዘልቁ አንድ አይነት ውቅር ታሪክ የሚጋሩና በተሳሰረ ግጭት ውስጥ የሚያልፉ ገፀ-ባህርያት በድርሰትሽ ውስጥ የየራሳቸውን መራራ እውነት ሲኖሩና የኑሮ ሀቃቸውን ሲተርኩ እየታዘብን ማለፋችን ህይወትን እነርሱን ሆነን መኖር ፤ በእነርሱው መነፀር ተመልክተን ሌላ ምስል መመልከትና እንግዳ ሀሳብን መታዘብ ያስቻለናል ብዬ ስለማምን ነው፡፡

ያው የለመድናቸው ፅሁፎች
አንድ ዋና ገፀ-ባህሪ ላይ ጥገኛ
ሆነው የተገደበና ነጠላ
( የአንድ ግለሰብ )ምልከታ ብቻ
የየሚያንጸባርቁ በመሆናቸው
ከአንባቢነት፣ ጠያቂነትና
የማስተዋል ትዝብት ይልቅ
በመሪው የልክነት ሚዛንና ሀቅ
ተወስነን ተቺ እና ፈራጅ
( judgemental )እንድንሆን
የሚያደርጉ ይመስለኛል!

  ባንቺ ድርሰት ውስጥ ግን
ሁሉም ገፀ-ባህሪያት
በየራሳቸው አለም ዉስጥ
ከየጓዳ 'ገመናቸው' ጋር
ስለቀረቡ ቢያንስ 'ወገን'
ከመምረጣችን በፊት ከ1 በላይ
የእይታ መነፀርን ልናጠልቅ፣
ብዙ ጓዳዎቻችን ልንታዘብ ግድ
ይለናል በሚል ነው፡፡

ርግጥ ነው የግድ 'ወገን'

መራጭ መሆንም ብቻኛ የንባብ የመጨረሻ ግብ ሆኖም አይደለም፤ እኔ እንደውም ባይሆን ከሚመርጡት ወገን ነኝ። ግን ቢያንስ ቢያንስ ለድምዳሜ ስንደረደር ወይም ለፍርድ ስንሮጥ 'ሌላውም ቤት ሌላ እውነት' መኖሩን በማሳየት ከራስ ጋር የመነጋገሪያ ድህረ ንባብ የጥሞና ጊዜ ይሰጠነናል ባይ ነኝ ( necessarily we don't hv to hv sides to stand by, we just can only be an observator. Actually thats the best thing to do as a reader, i believe! A loop hole to look for different n diversified opinions....so that we might start to think thinking different is nt a curse at ol, bt a blessing n a way forward! ) አዳም ረታን የምወደው ለዚህ ነው/በተለይ 'መረቅ'ን'

ሲፅፍ…አመሰግናለሁ!

ስለተጠቀምኳቸው የእንግሊዝኛ ቃላት በጣም ይቅርታ ፤ ሀሳቤን በተሻለ ይገልፃሉ በሚል ነው!

